## ፍትሕ አልባ ኢትዮጵያ

## ጸረ ሕዝቡ ወያኔ ወንጀለኞችን እለቃለሁ ብሎ ሲቀልድ፣ አርጀንቲና ግን አስሮ ለፍርድ አቀረበ

ከመላኩ ይስማው

**በአርጀንቲና በመፈንቅለ መንግስት ስልጣን ይዘው የነበሩ የጦር ሰራዊት መኮንኖች በተቃወማቸው ሕዝብ ላይ ፍጅት አካሂደው ለፈጸሙት ወንጀል ከወቅቱ ፕረዚዳንት ቪደላ ጀምሮ ለፍርድ እየቀረቡ ናቸው። የሚከተለውን ዜና ያንቡ፡**

### Former Argentine dictator Videla jailed for life

BUENOS AIRES (Reuters) - Former Argentine dictator Jorge Rafael Videla, who defends the campaign



of state violence that killed thousands of people from 1976 to 1983, was jailed for life on Wednesday for murder, torture and kidnapping.

Videla, 85, who has spent years in a military jail and under house arrest, repeatedly justified the brutality of the military junta in the so-called Dirty War crackdown on leftist opponents during his trial.

Human rights activists in the courtroom applauded when his sentence to a civilian prison was announced.

Rights groups say up to 30,000 people were kidnapped and murdered during the 1976-1983 dictatorship, which began when Videla and two other military leaders staged a coup on March 24, 1976.

When democracy returned to the South American country in 1983, Videla was sentenced to life imprisonment for the human rights crimes committed during his five years at the helm of the military junta.

But he spent just five years behind bars before being granted a pardon by then-President Carlos Menem. Eight years later, a judge scrapped Videla's pardon, ruling that the stealing of babies born to political prisoners constituted a human rights crime and was therefore imprescriptible.

In 2007, a court ordered him to serve the life sentence he was given in 1985 when Argentina tried the top dictatorship leaders. Wednesday's conviction is the first since he was pardoned by Menem.

World Cup cover

The families of the victims are being represented by Miguel Ceballos, a lawyer whose father was among those killed. "When they came looking for my father at the prison, he knew he would be killed," he said."He said goodbye to his friends and left a photo of his family so they could tell us what happened." During his five-year administration, Videla organized the 1978 World Cup in Argentina. Argentina's victory was used to try to clean the international reputation of the military government at a time when reports of massive human rights violations had been seeping out, our correspondent says.Videla also faces charges in Italy, Spain France and Germany for the murder of some of their citizens in Argentina.

ፍርደ ገምድሉ ወያኔ ግን ለይስሙላ ፍርድ ቤት ወንጀለኞችን አቀረብኩ/አስፈረድኩ ብሎ ከተመፃደቀ በኋላ ህግ ከሚለው ውጪ እነሆ ልፈታቸው ነው እያለን ነው። ይህ ሰሞኑን የሚናፈሰው የይቅርታ ወሬ በብዙ ምክንያቶች ይቅር መባባልን የሚያጠናክር ሳይሆን ቁርሾን የሚያባብስ ነው። ዋናው ነጥብ ፤ ሶስቱም ማለትም ይቅርታ የሚደረግላቸው፣ ይቅርታ የሚያደርጉት እና አስታራቂዎቹ — በቅደም ተከተላቸው የደርግ ባለሥልጣናቱ፣ ወያኔዎቹ እና የሃይማኖት አባት ነን ባዮቹ- - ሕዝብን ይቅርታ ሊጠይቁ የሚገባቸው ወንጀለኞች ናቸው። ህይወትን የቀነጠሱ፣ በውሸት በስብሰው፣ ሕዝብም ስለእውነት ለመናገር የሞራል መብታቸውን በልቦናው ከገፈፋቸው የቆዩ። አሁን እየፈፀሙ የአለው ስራቸውም በመንፈሳዊም ሆነ በምድራዊ የፍትህ ሚዛን ቢለካ ወንጀል ነው — ፍትህን፣ እውነትን የመግደል ቴአትር። ድርድራቸው ገዳይ ከገዳይ፣ ዋሾ ከዋሾ ነው።

ቀደምቶቹ የደርግም ሆነ የአሁኖቹ የወያኔ ገዳዮችና አፋኞች ልብ ሊሉት የሚገባው ባለፈው ጊዜ ለተፈፀሙ መጥፎ ሥራዎች ታላቁ የይቅርታ መጠየቂያ ቋንቋ በተከታይ በተግባር የሚታዩ ሥራዎች ናቸው። ፍትህን/እውነትን እየገደሉ በይቅርታ ስም መነገድም የበለጠ ግፍን ለነገ መዝራት ነው። ይቅርታ ሊሰጥ የሚችለውም ይቅርታውን ያስጠየቀው የግፍ ተግባር የተፈፀመበት ሰው ነው። ወይም ጉዳቱ የደረሰበት።

በወታደራዊው አገዛዝ በሕዝብ ላይ የተፈፀመውን ግፍ እንዲህ እንደቀላል - የእርስ በርስ መገዳደል አድርገው ሊያልፉት የሚሞክሩ አሉ። "ይቅር እንባባል" በሚል የፌዝ ሐረግም ሊያለባብሱት ይጥራሉ — ቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር በሚል። ማን ለምን መግደል ጀመረ የሚለውን አይነት የታሪክ ጥያቄዎች በዋናነት የሚመለከተው የፖለቲካ ድርጅት — ኢሕአፓ — መልስ ስለሰጠ/ወደፊትም ክርክር ሲነሳ የሚሰጥ ስለሚመስለኝ እኔ ብዙ አልልም። ግን እስኪ የሚከተለውን የታሪክ ቅንጫቢ ላፍታ እናስብ፡

*ከ1969 በፊት ደስተኛና ተጨዋች የሕይወት ዕቅድም የነበረው ወጣት ነው። አንድ ቀን በየካቲት ወር አጋማሽ ላይ ሰዎች ፍለጋ ይመጣሉ፣ ስድስት የአብዮት ጥበቃ ጓዶች፣ አንድ የሕዝብ ድርጅት ካድሬ ናቸው። ወጣቱ መደንገጡ ባይቀርም የፖለቲካ ሰው ባለመሆኑና በምንም ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ስለማያውቅ ያለምንም ችግር አስረድቶአቸው ነፃ እንደሚወጣ ገምቶአል። የኢህአፓ አባል የነበረው ወንድሙ የት እንዳለ እንደማያውቅና እሱ ግን በፖለቲካ ትግል ውስጥ ምንም ተሳትፎ የሌለውና ወደፊትም የማይፈልግ መሆኑን ለማስረዳት ሞከረ። ወጣቱ ያላወቀው ጉዳይ አሳሪዎቹ ራሳቸው ይህን እንደሚያውቁ ነው። ለማንኛውም በታሰረ በሁለተኛው ቀን እጅግ የሚዘገንን ሽታ ወዳለው አንድ ክፍል ውስጥ ሲያስገቡት ወንድሙን እዚያ አገኘው። ወንድሙ ሲገረፍና በምድር ላይ ያለው አካላዊ ስቃይ ሲደርስበት ስለነበር መልኩ ሁሉ ተለውጦአል። አሁን ደግሞ እሱ ተረኛ ሆነና ከታላቅ ወንድሙ ፊት ያሰቃዩት ጀመር። የሚያሰቃዩት ሰዎች የሚፈልጉትን ወንጀል ሁሉ ለማመን ዝግጁ መሆኑን እየገለጠ በደከመ አንደበት ቢማፀንም ሥቃዩ ቀጠለ።*

*ከሳምንት በሁዋላ እናታቸው ተይዘው መጡ። በ60 ዓመት ዕድሜ የሚገመቱ እናታቸው የፈጫይ ፈጭተው፣ የፈታይ ፈትለው ካሳደጉአቸው ልጆች ጋር ተቀላቀሉና ልጆቻቸውን ሲያዩ መሬሹ ጀመሩ። ይህ የመንፈስ ስቃይ መጀመሪያቸው ነበር። ምስኪንዋ እናት በልጆቻቸው ፊት ልብሳቸውን እንዲያወልቁ በሥፍራው በነበሩት ስድስት መርማሪዎች ይታዘዛሉ። ይገረፋሉ። ይሰቃያሉ። በዚህም ጊዜ ቢሆን ትልቁ ልጅ አንዳችም ቃል አልተነፈሰም። የኢህአፓ አባልነቱን አላመነላቸውም። በመጨረሻ መርማሪዎቹ ብልቱን ቆርጠው ከከተፉ በሁዋላ እናቲቱን አበሉዋቸው። ሴትዮዋ ወዲያው ህሊናቸውን ሳቱና ከሥር ቤት ሲወጡ ራሳቸውን ገደሉ።* (የሚያነቡ እግሮች፣ ገጽ 43)

ሌሎችም ብዙ ብዙ ሰቅጣጭ ወንጀሎች አልተፈፀሙም እንደ? እንደ ዳሮ ነጋሽ ዓይነቶቹ በነበራቸው የሙያ ማህበርም ሆነ የፖለቲካ ተሳትፎ እየተያዙ የተረሸኑት፣ ከእነሱም አልፎ ቋጥረውት የነበረው ሽል ሳይቀር ሆዳቸው ተቀዶ እየወጣ የተገደሉት በግፍ አይደለምን? ዜጎች እንደ ሻሸመኔዋ ባለሆቴል እናት ከየቦታው እየተያዙ በጥይት ተደብድበው፣ ነፍሳቸው ሳትወጣ አፈር የተመለሰባቸው መሆኑ ግፍ አይደለምን? በጅማ ነፍሰ ገዳዩ ዓሊ ሙሳ አንድ ነፍስ ያላወቀ ልጅ ጠርቶ ግርግዳ ላይ የተፃፈ "ኢሕአፓ ያቸንፋል!" የሚል መፈክር አንብብ በማለት አዞት፣ ማንበብ ሲጀምር እና ሶስተኛውን "አ" ፊደል ለመናገር አፉን ሲከፍት፣ በአፉ እስከ መረቁ ተኩሶ እንደገደለው፣ የዜጎችን ህይወት የግድያ፣ የስካር ወዘተ ማርኪያ ማድረግ ግፍ አይደለምን?

ሚስትን ንብረትን ለመቀማት ዜጎችን መግደል ማሰር ግፍ አይደለምን? ከየቤቱ፣ ከየመስሪያ ቤቱ፣ ከየመንገዱ፣ ከየቦታው ዜጎችን እየያዙ መጨፍጨፍ ግፍ አይደለምን?

ለመመርመር እና  አስሮ የእርማት እርምጃ ለመውሰድ አቅም የነበረው ወታደራዊው አገዛዝ የተቃዋሚው (ባብዛኛው የኢሕአፓ) አባል ናቸው ብሎ የጠረጠራቸውን ዜጎች እያፈሰ ሲያስርና እያወጣ በጅምላ ሲያሰቃይ፣ ሲረሽን፣ ኢሕአፓ የመከላከል እርምጃ ከመውሰዱ በፊት አባላቱን ለሚያሳድድበት የመንግስት ሰው በተደጋጋሚ እባክህ ተወን ማስጠንቀቂያ ይሰጥ የነበር መሆኑንም እናውቃለን። እና ያን በፍፁም! በፍፁም የማይመጣጠን በአገዛዙ የተከናወነ ጭፍጨፋና እመቃ እንዲህ አቃሎ ለመሸፋፈን መሞከር ለሀገራችን፣ ለህዝባችን ፍውሰትን አያመጣም።  እውነቱን ተቀብለን ግፍን በግፍነት መውሰድ መቻል አለብን።  ይፈታሉ የሚባሉት የደርግ ባለሥልጣናቱም ሆነ ደጋፊዎቻቸው ይህ ዘግናኝ ክስተት በሀገራችን መፈፀሙን አምነው በሙሉ ልብና ዓይን ከታሪክ ፍርድ ችሎት ቀርበው ሕዝብን ምህረት ሲጠይቁ  አላስተዋልንም።  ትላንት የገደሏቸውን ዜጎች ታሪክ  ዛሬም ዳግም በውሸት እና በእርስ በርስ ተገዳደልን ስም ሊገሉ ሲጥሩ እንጂ። የወቅቱ ትግል መሪ ጥያቄዎች  - ሕዝባዊ መንግሥት!  የፖለቲካ ድርጅቶች ይፈቀዱ! የመደራጀት፣ የመሰብሰብ ወዘተ መብት ይከበር!  -  ህዝባዊ መሠረት የነበራቸውና አሁንም ያልተመለሱ መሆናቸውን በእውነት ስለእውነት አይናዘዙም።

በዚሁ የይቅርታ ቴአትር ውስጥ የይቅር ባይነቱን ትዎና የሚጫዎተው ወያኔም ቢሆን መጀመሪያ ንሥሃ መግባት ያለበት ወንጀለኛ ነው።  ደርግ በከተማ ሲጨፈጭፍ ወያኔ በትግራይ ገጠሮች በግልጽ፣ በሌሎችም ቦታዎች ከወታደራዊው መዋቅር ጋር ተዳብሎ በመግባት በውስጥ ለውስጥ ዜጎችን ፈጅቷል፣ አስፈጅቷል።  ወደሥልጣን ከመጣም በሁዋላ ትላንት ወታደራዊውን አገዛዝ ሲታገሉ፣ መከራ ሲቀበሉ የነበሩ የሕዝብ ልጆችን አርዷል — ተስፋዬ ታደሰ፣ ጋይም ወዘተን ይጠቅሷል።  ሌሎችንም — ደብተራው፣ አበራሽ፣ ይስሃቅ፣ ስጦታው፣ ወዘተ — ለዓመታት አፍኖ የት እንዳደረሳቸው አይታወቅም።  ትላንት በወታደራዊው አገዛዝ ቀይ ሽብር በግንባር ቀደምነት ታውጆበት ሲጨፈጨፍ፣ ሲሳደድ የነበረውን ኢሕአፓ፣  ዛሬም ወያኔ በደህንነት መስሪያ ቤቱ ውስጥ እራሱን የቻለ መምሪያ አቋቁሞ ይጨፈጭፈዋል፣ ያሳድደዋል፣ ሊያጠፋው ይጥራል። ታዲያ በትላንት መቃብር ላይ ዛሬም ትኩስ እሬሳ የሚጨምር፣ በትላንት እስር ቤቶች ውስጥ ዛሬም ትኩስ እስረኞች የሚያጉር ቂመኛ፣ ቁርሾ ሰሪ፣ መሰሪ ወያኔን መሰል ድርጅት እንደምን ይቅር ባይ ሊሆን ይችላል?  ለመሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠረውን አብዛኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ በጨቋኝ አገዛዙ የሚያሰቃየው ወያኔ ከሃያ የማይበልጡ የደርግ ሰዎች በመፍታት ምን ዓይነት እርቅ፣ ምን ዓይነት ለውጥ ነው የሚያመጣው?  ለፖለቲካ ፍጆታው ካልሆነ በስተቀር — በተለይም ባዕዳን ለሚያዩለት የውጭ ዕይታው።

እነ አባ  ኣምሓየስን ለእስር የዳረገው አባ ገብረመድህንና መሰሎቹ ደግሞ ለወያኔ ሲጸልዩ ቆይተው ዛሬ ለወንጀለኞች መፈታት እርቅና ሰላም ሰባኪ መሆናቸው ያስገርማል። ከዓመታት በፊት እነ አበራ የማነአብ ለሰላምና ዕርቅ ጉባኤ አዲስ አበባ ሄደው ከቦሌ ሲታሰሩ ይህ የወያኔ ጳጳስ ለውጥ የመጣባችሁ ብሎ ማውገዙ የሚታወስ ነው።  ይኸው ጳውሎስ አይደለም እንደ ካመታት በፊት "ማን ተጣላና ነው፣ እርቅ እርቅ የሚባለው?!" በማለት የተቃዋሚዎችን ጥሪ ያጣጣለው?  ይኸው ጳውሎስ አይደለም እንደ ባሕታዊውን (ፍቃደ ሥላሴን)፣ በቤተክርስቲያን ገረገራ ላይ የገደለው/ያስገደለው?  ይኸው ጳውሎስ አይደለም እንደ ከወያኔ አፋኞች ሸሽተው ቤተክርስቲያን የተጠለሉትን ተማሪዎች አሳልፎ የሰጠው?  የዚሁ የካቶሊካዊው ሰው የጳውሎስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ ጳጳስ ሆኖ በሕገወጥ መንገድ መሾም፣ ከተሾመም በሁዋላ የሚፈጽማቸው ከቀኖና ውጭ የሆኑ ድርጊቶቹ  አይደሉም እንደ  ቤተክርስቲያኗን የሚያምሷት?  እነኝሁ ለወያኔ ፖሊተካዊ ፍጆታ የሚውል ጥቅም ለማስገኘት እናስታርቃለን የሚሉት የሃይማኖት አባት ተብዬዎችም ሆኑ ስመ ሽማግዎች በዚህ ድርጊታቸው ከማህበረሰቡ ከበሬታን ሳይሆን ትዝብትን ነው እሚያተርፉት። ገና ከጅምሩ የሃይማኖት አባት ነን የሚሉት ሰዎች አነጋገርናቸው ያሏቸው የቀይ ሽብር ተጎጂ ቤተሰቦች ውሸት መሆኑን ገልጸው ለባሰ ትዝብት ጥለዋቸዋል።  የደርግ ጭፍጨፋ ዋና ሰለባ የሆነው ኢሕአፓም ተቃውሞውን በመግለጫ ገልጿል።

እነኝሁ ሽማግሌ ነን ባዮቹ መጀመሪያ ከራሳቸው ሊታረቁ ይገባል — የውስጥ ነፍሳቸው ከሚያውቀው እውነታ ጋር እርቅ ማውረድ አለባቸው — ልቦናቸው ያውቀዋልና።  በየሃይማኖት ክፍላቸው ያለውን መከፋፈል፣ መቃቃር ሲያፀዱ፣ እርቅ ሲያወርዱ፣  ሃይማኖታቸው የሚከለክላቸው ኢሰብአዊ ድርጊቶች ለምሳሌ መግደል፣ መግረፍ፣ ማፈን፣ በድህነት ማቆራመድ ወዘተ የመሳሰሉት  መፈፀማቸውን ሲቃወሙ፣  ለሰው ሰውነት መከበር ሲቆሙ፣ ያንዬ ህዝቡ አሁን የነሳቸውን የሽምግልና ሞራላዊ ብቃት ይሰጣቸዋል።

እነሱም በማህበረሰቡ አባታዊ ክብርን ሲጎናፀፉ፣ የደርጉ አገዛዝ ባለሥልጣናትም ሆኑ አሁን ያንኑ የነበረ ገዳይ ሥርዓት ያስቀጠሉት የወያኔ ወንጀለኞች እስከዚያ ጊዜ ድረስ የሰሩትን ወንጀል ሲናገሩ፣ የግፉ ሰለባ የሆኑትንም በፀፀት ይቅርታ ሲጠይቁ፣ የቀሙትን የሕዝብ ሥልጣን ለሕዝብ ሲመልሱ ነው እውነተኛ እርቅ።  ሕዝብን ያሳተፈ፣ ሕዝባዊ የሥልጣን ባለቤትነትን እውን ማድረግን ያካተተ ሲሆን ነው እርቅ እውነተኛ እርቅ የሚሆነው።  የደቡብ አፍሪካም ልምድ ቢሆን ከሞላ ጎደል ይህንኑ ነው የሚያመሳክርልን።